VOTE 2024

# የድምጽ ሰጪዎች ቋንቋ

የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ጽህፈት ቤት | 1-877-600-VOTE | mnvotes.gov

## ምርጫ የሚካሄድባቸው ቦታዎች

ለሁሉም የክፍለሃገር ምርጫዎች፤ በምርጫው ዕለት የሚያገለግሉ የድምጽ አሰጣጥ መመርያዎች፤ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ሌላ፤ በሚዘወተሩት ሶስት ቋንቋዎች በአሁኑ ግዜ ተዘጋጅተው ይቀርባሉ።

በአሁኑ ወቅት ሶስቱ ቋንቋዎች የሚከተሉት ናቸው፡

- ስፓኒሽኛ
- ህሞንግ
- ሶማሊኛ

ሰዎች ለምርጫ በየምርጫ ጣብያው ሲሄዱ ***"እንዴት መምረጥ እንደሚቻል"*** የሚል መመርያ በሶስቱ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ያገኛሉ። **እነኚህን መመርያዎች እንዴት እንደሚያገኙም በእነዚሁ ሶስት ቋንቋዎች የተተረጎመ ጽሁፍ ያገኛሉ።**

ተጨማሪ የተተረጎሙ ፖስተሮችም (ሰሌዳዎች) በየምርጫው ጣብያ ለማጣቀሻ የሚሆኑ ይቀርባሉ። እነኚህ ፖስተሮች በሙሉም ከምርጫው ጣብያ ዌብፔጅ (webpage) ሊገኙ ይችላሉ።

## የምንጮች ማገናኛያ (LINKS)

**የምርጫ ጣብያ ፖስተርስ፡**
www.sos.state.mn.us/election-administration-campaigns/election-administration/polling-place-posters

**የአውራጃ የቋንቋ አናሳ (MINORITY) የሰሌዳ ወረቀት፡ (SPREADSHEET)**
www.sos.state.mn.us/media/5634/language-minority-districts-tracts-precincts-languages.xlsx

**የቋንቋ ትርጉም አገልግሎት የሚጠየቅበት ፎርም፡**
www.sos.state.mn.us/media/5633/request-for-interpretive-services.pdf

## የተመደቡ የአናሳ ቋንቋ አውራጃዎች

የአገር ውስጥ ጉዳይ (Office of the Secretary of State) ጽህፈት ቤት ከክፍለሃገሩ የስነ-ህዝብ ተመራማሪ (Demographer) ጋር በመተባበር፤ ከሶስት ከመቶ ወይም ከዛ በላይ የእንግሊዘኛ ቋንቋ በደንብ የማይችሉ ሰዎች ያሉባቸው አውራጃዎች የትኞቹ እንደሆኑ ለማወቅ ሰርቷል። **ቋንቋ የማይችሉ የአናሳ አውራጃዎች የሰሌዳ ወረቀት** የተመደቡ አጫጭር ጽሁፎች አሏቸው-ለእያንዳንዱ ቋንቋ ከ3% ወይም ከ20% ድረስ ያለው የቋንቋ እጥረት አሟላ አላሟላ፤በሁሉም ቦታዎች ላለው ጽሁፍ ተመድቦለታል።

የቋንቋ እጥረት ባሉባቸው አውራጃዎች ሁሉ፤ የምርጫ መመርያዎችና ለምሳሌ የቀረቡ የምርጫ ወረቀቶች በቦታዎቹ በሚዘወተሩት ቋንቋዎች ተተርጉመው ቀርበዋል። እነኚህ የምርጫ መመርያዎችና የምሳሌ ወረቀቶች፤ ሰዎች ድምጻቸውን ለመስጠት በሚመጡበት ቀን እንዲረዷቸው ተዘጋጅተው ይጠብቋቸዋል።

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ፤ በአንድ አካባቢ ውስጥ ከ20% ወይም ከዛ በላይ የእንግሊዘኛ ቋንቋ የማይችሉ መራጮች ካሉ፤ አስር ወይም ከዛ በላይ የሆኑ የተመዘገቡ መራጮች፤ በምርጫው ቦታ ለመራጮች አስተርጓሚ እንዲደርግላቸው የአገር ውስጥ ጉዳይ ክፍልን ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህንን ጥያቄ ለማቅረብ የሚሞላ **የአስተርጓሚ አገልግሎት መጠየቅያ ፎርም** አለ።

ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ወይም ድርጅቶች፤ የቋንቋ እጥረት አለበት ተብሎ ቀደም ሲል ባልተመደበ ቦታ፤ የጹሁፍ ወይም የቃል ትርጉም አገልግሎት ያስፈልጋል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፤ ይህንን መረጃ ለአገር ውስጥ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ወይም ለአውራጃቸው ኦዲተር ሊያቀርቡ ይችላሉ። ጉዳዩ ከተጠናና ተቀባይነትን ካገኘ በኋላ አስፈላጊው የጹሁፍ ወይም የቃል ትርጉም አገልግሎት በተግባር ላይ እንዲውል ይደረጋል።

**ይህንን ኮድ ይቃኙ (Scan) ፤ የሚከተለውን ለመጎብኘት የድምጽ ሰጪዎች መዳረሻ (VOTER LANGUAGE ACCESS) ገጽ ለተጨማሪ መረጃ**